# እስከ መቸ!

“ኣርሼ ልብላበት፣ ኣፈር ጭሬ፣ ግሬ
“ተዉ ኣትነካኩኝ” ለሚለው ገበሬ
ጠላት ኣሰባስበው ከሩቅና ቅርብ
ምክንያት ፈልገው፣ ኃይማኖት ሰበብ
        ቸኰሉ ሊዘምቱ!
ኢትዮጵያ መቸ ዋዛ ፣ ልጆቿ ኣይፈቱ!
        የሸርማርኬ ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
        ጅሃድ ኣወጁባት ውዷቷ ሃገሬ!

የወንበዴ ኣገር፣ የሌለው መንግሥት
ሲታመስ፣ ሲያምሱት ለዓሥር ዓመታት
እስርስ በራሳቸው ሲጣሉ፣ ሲባሉ
የኢትዮጵያን መሬት ሊቀሙ ከጀሉ
        ኣወይ ሞኝነት!
እንዲህ በቀላሉ ኣይገኝ መሬት
        የሸርማርኬ ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
        ጅሃድ ኣወጁባት በውዲት ሃገሬ!

ኣንድ በጥባጭ ካለ ንጹሕ ማን ይጠጣል
ምን ሰላም ይገኛል፣ ሁሉ ይበጠበጣል
ከሶርያና ከግብፅ፣ ዓረብ፣ ፓኪስታን
ተጠራርተው መጡ፣ ኣልቀረም ኢራን
        ኣሁን ምን ይባላል!
“ኑ! ለፀሎት” ያለው ኣይስማ ቢላል!
        የሸርማርኬ ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
        ጅሃድ ኣወጁብሽ ውዷቷ ሃገሬ!

ሰማንያ ሚልዮን ሕዝብ በጥቂት ወንበዴ
እስከ መቸ ድረስ ይታመሳል እንዴ!
“…ሰላም ኣስተናግዳን፣ የፍትሕ ኣገር ናት
ኢትዮጵያን ኣትንኩ፣ የሰው ልጆች እናት…”
        ብሎ ቢነግራቸው
ነብዩን ከመስማት፣ ሰይጣን መካሪያቸው፣
        የሸርማርኬ ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
        ጅሃድ ኣወጁባት በውዱ ሃገሬ!

ይኽ ኣዲስ ኣይደለም፣ የቆየ ነው ጥንት
ዘልዓለም ሲያምራቸው የሃገሬ መሬት
ሓሸዋና ሓሩር ውሃም የለበት
ቀና ቢሉ ሰማይ፣ ጐንበስ ሲሉ እሳት
    ሳንደርስባቸው!
ደረቅ ምድረ-በዳ ሆነና ኣገራቸው
    የሸርማርኬ ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
    ጅሃድ ኣወጁባት በውዲት ሃገሬ!

እንደ ሃዬ ካሌብ፣ እንደነ ኤዛና
ውጣ! ዝመትበት! በለው! በለውና!
ኣንዲትም ጠመንጃ፣ ኣንዲትም ጥይት
ዘልቃ እንደማትገባ ከሩቁ ጠላት
    እስከ መቸ ድረስ!
ሰማንያ ሚልዮን ሕዝብ በነዚህ ይታመስ
    ኣያዳግም ሥራ ዛሬ ነው መሥራት
ለነገው ሰው ሰላም እንዲሆንለት

ግመል የረገጠው፣ የሄደበት ሁሉ
ሶማል ነው፣ የኛ ነው፣ እንውሰደው ካሉ
ከቅኝ ግዛት በፊት፣ ከእንግሊዝ፣ ኢጣልያ
ኣሁን በጠቅላላው የሚሉት “ሶማልያ”
    ታሪኩ ይመርመር!
የባሕር ጠረፉስ እስኪ የማን ነበር?
    ኣያዳግም ሥራ መሥራት ነው በዚያው
    ባሕር ጠረፉንም ዘለቀን እንያዘው።

ኣንፈልግም ካሉ ሰላም፣ መስማማቱ
እነሱ ካወጁት ቀድመው ጦርነቱ
ተነሱ፣ እንነሳ ለውድ ሃገራችን
መስዋእት ይሁንላት፣ እናፍስስ ደማችን
    ፈጥኖ መታጠቅ!
ለልጅ ልጆቻችን ሰላም እንዲዘልቅ
    የሸርማርኬን ልጆች፣ የነሰይድ-ባሬ
    ቆራርጠን እንጣል ከቀይ ባሕር ኩሬ

ገ/ኢ. ጐርፉ።